
# ምዕራፍ ሦስት

## እኩልነት ምንድነው?




**የሚጠበቁ ውጤቶች:**


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤

- ❖ ስለእኩልነት ምንነት፣ መሠረታዊ ባሕርያትና መርሖች ደረጃውን በጠበቀ የኢ.ምቋ ታስረዳላችሁ፤
- ❖ ከእኩልነት ጋር የተያያዙ የኢ.ምቋ ምልክቶችን ከነሥነምልክታዊ ውበታቸው በዕለት-ተዕለት ተግባቦት ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤
- ❖ ከንባብ ውስጥ ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ትለያላችሁ፤
- ❖ የምዕራፉን ቁልፍ ምልክቶች በራሳችሁን ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተገቢው መንገድ መጠቀም ትጀምራላችሁ፤
- ❖ የአያያዥ ምልክቶችን የኢ.ምቋን ሥርዓት በተከተለ መንገድ በዕለት-ተዕለት ተግባቦት ውስጥ መጠቀም ትጀምራላችሁ፤
- ❖ የኢ.ምቋ ምልክቶችን ሥነምልክታዊ ባሕርያትን መሠረት በማድረግ ትተነትናላችሁ::

## ቁልፍ ምልክቶች




ዘር



ፆታ



ሕግ




ማህበራዊ




ኢኮኖሚ




ህብረተሰብ




ተሳትፎ




ተጠቃሚ





ገጠር





አመለካከት


የተዛባ



ስርየሰደደ



አሉታዊ



አቻ


መገለል


መሻት


ምንድን ነው


እኩልነት


አካልጉዳት


## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ዕይታዊ ንባብ

1. የሚከተለውን ሥዕል በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ።
2. ሥዕሎቹ ስለ እኩልነት ምን ይናገራሉ?







## ክፍለ ትምህርት ሁለት

### ንባብ

### የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

1. በአካባቢችሁ የነዋሪዎችን ሁሉ እኩልነትን ለማስከበር መንግሥት የወሰዳቸውን እርምጃዎች ወይም ያወጣቸውን ሕግጋት ጥቀሱ።
2. በትምህርት ቤታችሁ የሁሉም ተማሪዎች እኩልነት ተከብሯል? መልሶቻችሁን የሚደግፉ ምሳሌዎች ጥቀሱ።
3. የክፍል ጓደኞቻችሁን እኩልነት የምታከብሩት በምን መንገዶች እንደሆነ አብራሩ።

መምህራችሁ «እኩልነት ምንድነው» የሚለውን ንባብ ሲያነቡ፣ ሐሳቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን-ለጎን የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቀቄ ተመልከቱ።

## እኩልነት ምንድነው?

እኩልነት የሰው ልጆች እስከ መስዋዕትነት ድረስ የታገሉለትና እየታገሉለት ያለ የሰው ልጆች መሠረታዊ ጥያቄ ነው። እኩልነት በትርጉምም በአተገባባርም ሊለያይ ይችላል። ለምሳሌ፣ የዕድሜ እኩልነት፣ የጾታ እኩልነት፣ ፖለቲካዊ እኩልነት፣ ወዘተ፣ አለ። እኩልነት በተለያዩ አገባቦች ውስጥ የተለያዩ ትርጉሞች ስለሚኖሩት፣ አንድ ትርጉም መስጠት ያስቸግራል። ለምሳሌ፣ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስቱን የእኩልነት ዓይነቶች ብንወስድ፤ የዕድሜ እኩልነት ተመሳሳይ ቁጥር ያለው የዕድሜ እርከን ላይ መገኘትን ሲያመለክት፣ የጾታ እኩልነት ደግሞ ወንድና ሴት እኩል መብት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ያሳያል። ፖለቲካዊ እኩልነት ደግሞ የዜጎች ሁሉ በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን የሚጠቁም ነው።

በሀገራችን እንደአገባባቸው ተተርጉመው በዘልማድና በሕግ እንዲከበሩ የተደረጉ ብዙ እኩልነቶች አሉ። የዕድሜ እኩልነት ማለት ሁለት ሰዎች በተመሳሳይ የዕድሜ እርከን ላይ ይገኛሉ ማለት ነው። በባህላችን በተለያዩ የዕድሜ እርከኖች ላይ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ እኩል ተደርገው እንዲታዩ አያበረታታም። ዕድሜን መሠረት ያደረገው እኩልነት በተመሳሳይ የዕድሜ እርከን ላይ ለሚገኙ ሰዎች ብቻ ያገለግላል። እነዚህ ሰዎች የዕድሜ እኩዮች ይባላሉ።

ጾታዊ እኩልነት ማለት ሴቶችም ወንዶችም በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ እኩል ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መብቶች አሏቸው ማለት ነው። ወንዶች መማር፣ መሥራት፣ መዝናናት ወይም የፈለጋቸውን መርጠው የማግባት መብት እንዳላቸው ሁሉ ሴቶችም ተመሳሳይ መብት አላቸው ማለት ነው። ይህ እኩልነት ለዘመናት የተንሰራፋውን ሴቶችን ከወንዶች ዝቅ አደውርጎ የማየት ሁኔታን የሚቃረንና፣ ሁለቱም ፆታዎች እኩል የመብት ተጠቃሚ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ነው። ይህም ሴቶችን የወንዶች ብቻ መብቶች እንደሆኑ ተደርገው ሲታዩ ከነበሩ መብቶች ሙሉ ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማድረግ ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ መንገድ ሲታይ በወንዶችና በሴቶች መካከል እኩልንት ሊኖር ይገባል።

ፖለቲካዊ እኩልነት ማለት ሁሉም ዜጎች በብሔር፣ በሃይማኖት፣ በፆታ፣ በዕድሜ፣ በአመለካከት፣ በአካል ጉዳት፣ በቋንቋና በመሳሰሉት ልዩነት ሳይደረግባቸው የእኩል መብት ባለቤቶች ናቸው ማለት ነው። የኢፌድሪ ሕገመንግሥት ሁሉም ዜጎች በሕግ ፊት እኩል መሆናቸውን ያረጋግጣል። ሁሉም ዜጎች የመምረጥና የመመረጥ፣ በነጻነት የመኖር፣ የመሥራት፣ ሀብት የማፍራት፣ የሃይማኖት ሥርዓቶችን መፈጸም፣ ቋንቋቸውን የመጠቀም ወዘተ፣ እኩል መብት አላቸው። ለምሳሌ ዓይነ-ስውራንና (መስማት የተሳናቸውና) ጆሮ-ሰሞች (መስማት የሚችሉ) እኩል መብት አላቸው ማለት ነው። ትምህርት፣ መረጃ፣ ወዘተ፣ ለዓይነ-ሰሞችም ለጆሮ-ሰሞችም እኩል ተደራሽ ማድረግና ሁለቱም ተምረውና ሰርተው ለማደግ የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ ማድረግ ማለት ነው።

የእኩልነት መርሖች መከበር ለሕዝቦች ሠላማዊ አብሮነትና ለፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ቁልፍ ሚና አለው። እኩልነት እርስበእርስ መከባበርንና ልዩነትን መቀበልን ስለሚያበረታታ የእርስ በእርስ ግጭቶች እንዳይፈጠሩ ይከላከላል። እኩልነት በተከበረበት ሀገር ሰዎች ሐሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ፣ መብቶቻቸውን የመጠየቅ፣ የጋራ ሀብት ተጠቃሚ የመሆን፣ ወዘተ፣ ዕድል ስላላቸው በአመጽና በወንጀል ድርጊቶች የመሳተፍ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ ይሆናል።

## መልመጃ አንድ

**የሚከተሉት በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ።**

1. በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበበላችሁ ንባብ ተወስደው ወደ ኢምቋ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢምቋ አንብቡ።
2. መጽሐፎቻችሁን ሳትመለከቱ፣ የምንባቡን መልዕክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ ውስጥ በኢምቋ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

**የሚከተሉትን ከምንባቡ ውስጥ የወጡ ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ።**

1. ፖለቲካዊ እኩልነት ምን ማለት ነው?
2. የዕድሜ እኩልነት ማለት ምን ማለት ነው?
3. ባህላችን ሰዎች ሁሉ እኩል አይደሉም የሚለው ምን መሠረት በማድረግ ነው?
4. በሀገራችን ፖለቲካዊ እኩልነት ለማስፈን ከተወሰዱ እርምጃዎች ውስጥ አንድ ምሳሌ ጥቀሱ።
5. ዓይነ-ሰሞችና (መስማት የተሳናቸውና) ጆሮ-ሰሞች (መስማት የሚችሉ) ምሳሌ በማድረግ ፖለቲካዊ እኩልንትን አብራሩ።
6. የእኩልነት መርሖች መከበር የእርስ በእርስ ግጭቶች እንዳይፈጠሩ የሚከላከለው እንዴት ነው?
7. እኩልነት በተከበረበት ሀገር ሰዎች በአመጽና በወንጀል ድርጊቶች የመሳተፍ ፍላጎታቸው ዝቅተኛ ይሆናል። እንዴት? አብራሩ።

# መልመጃ ሦስት

## ዐረፍተ ነገር ምሥረታ


**የሚከተሉትን ቃላት የሚወክሉትን ምልክቶች በመጠቀም የተሟሉ ዐረፍተ ነገሮችን በኢምቋ በመመሥረት በክፍል ውስጥ አሳዩ።**

1. ተሳተፎ
2. የተዛባ
3. አሉታዊ
4. አመለካከት
5. እኩል ጊዜት

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## የምልክቶች ትንተና

**ቀደም ባሉት ክፍሎች በተማራችሁት መሠረት፣ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የተማራችኋቸውን ዋና-ዋና ምልክቶች ትንተና በክፍል ውስጥ አሳዩ።**



ለምሳሌ፡- ዘር

1. የእጅ ቅርጽ፡ ዘ የእጅ ቅርጽ
2. የእጅ ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ፡ በባዶ አየር
3. የመዳፍ አቅጣጫ፡ ወደ ውስጥ
4. የእጅ እንቅስቃሴ፡ በክብ መልክ ወደ ፊት
5. በእጅ የማይገለጹ ክፍሎች፡ ነፃ

# ክፍለ ትምህርት አራት

## አያያዥ ምልክቶች

አያያዥ ምልክቶች የምንላቸው ምልክቶችን ከምልክቶች፣ ሐረግን ከሐረግና ዐረፍተ ነገርን ከዐረፍተ ነገር ለማያያዝ የምንጠቀምባቸው ናቸው።

**ምሳሌ**

*ግን፣ እና፣ ምክኒያቱም፣ እንዲ፣ ስለዚህ፣*

| | |
|---|---|
| ኢ.ምቋ፡ | ወንድ ሴት ሕግ እኩል ተረጋገጠ ጨረሠ ግን አፈፃጸም ችግር |
| አማርኛ፡ | የወንዶችና የሴቶች እኩልነት በሕግ የተረጋገጠ ቢሆንም የአፈጻጸም ችግር አለ። |
| ኢ.ምቋ፡ | በደንብ ማንበብ ጨረሰ ግን ፈተና ወደቀ |
| አማርኛ፡ | በደንብ አንብቤያለሁ ነገር ግን ፈተና ወደቅሁ። |
| ኢ.ምቋ፡ | ዛሬ ጠዋት ማታ ቤት ቆየ ምክንያት ምን- ሥራ የለም። |
| አማርኛ፡ | ዛሬ ሥራ ባለመኖሩ ምክንያት ከቤት ዋልኩ። |

## መልመጃ አንድ

**ከላይ በተሰጠው ምሳሌው መሠረት፣ የሚከተሉትን አያያዥ ምልክቶች በመጠቀም፣ በኢምቋ ዐረፍተ ነገር መሥርተችሁ በክፍል ውስጥ አሳዩ።**

1. ስለዚህ
2. ግን
3. እና
4. ምክንያት
5. እንዲ

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## የኢምቋ ሰዋስው ናሙናዎች ልምምድ

**የተሰጡትን ናሙናዎች በጥንቃቄ ከተለማመዳችሁ በኋላ፣ ከላይ ስለእኩልነት የቀረበውን ንባብ በኢምቋ አንብቡ።**

ኢምቋ፡ እኩልነት ሰው ብዙ ዓመት መስዋዕት መሆን ድረስ መታግል መታገል ሰው ዋና ጥያቄ

አማርኛ፡ እኩልነት የሰው ልጆች መስዋዕት እስከመሆን ድረስ የታገሉለትና እየታገሉለት ያለ የሰው ልጆች ዘመን የተሻገረ ጥያቄ ነው።

ኢምቋ፡ እኩልነት አንድ አይደለም ትርጉም ተግባር ልዩ ልዩ አለ

አማርኛ፡ እኩልነት በትርጉምም በአተገባበርም የተለያየ ዓይነት አለ።

ኢምቋ፡ እኩልነት ልዩ ልዩ አገባብ ልዩ ልዩ ትርጉም አለ አንድ ትርጉም ብቻ መስጠት ከባድ

አማርኛ፡ እኩልነት በተለያዩ አገባቦች ውስጥ የተለያዩ ትርጉሞች ሊኖሩት የሚችል ቃል ስለሆን አንድ ትርጉም መስጠት ያስቸግራል።

ኢምቋ፡ ዕድሜ እኩል አንድ፣ ፆታ እኩል ሁለት ፖለቲካ እኩል ሦስት ልዩ ልዩ እኩለ አለ

አማርኛ፡ የዕድሜ እኩልነት፣ የጾታ እኩልነት፣ ፖለቲካዊ እኩልነት ወዘተ፣ አለ።

ኢምቋ፡ እኩል ዕድሜ ማሳየት ምን ተመሳሳይ ዕድሜ ቁጥር ጾታ እኩል ማሳየት ምን ወንድ ሴት እኩል መብት አለ

አማርኛ፡ የዕድሜ እኩልነት ተመሳሳይ ቁጥር ያለው የዕድሜ እርከን ላይ መገኘትን ሲያመለክት የጾታ እኩልነት ደግሞ ወንድና ሴት እኩል መብት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ያሳያል።